Employment Security Department
WASHINGTON STATE

# COVID-19 (ኮሮናቫይረስ) ሳምንታዊ የይገባኛል ጥያቄዎች

የአደጋ ጊዜ ህጎች በCOVID-19 ለተጎዱ ሰራተኞች እና አሠሪዎች ተወስደዋል። በCOVID-19 ገጽ ላይ የበለጠ ይወቁ።

***አስፈላጊ መረጃ August 5, 2020 ቀን ተዘምኗል)***

- የአስቸኳይ ጊዜ የCOVID-19 ህጎች መከኒያት March 8, ቀን 2020 ዓ.ም ወይም ከዚያ በኋላ ለቀረቡት የይገባኛል ጥያቄዎች "waiting week" (የጥበቃ ሳምንት) ተዘዋውሯል።
- የሥራ ፍለጋ አሁን አማራጭ ነው። ምንም የፍለጋ እንቅስቃሴዎችን ሪፖርት ማድረግ የእርስዎን ጥቅም አያዘገይም።
- በመስመር ላይ ፋይል ማድረግ ከስልክ የበለጠ ፈጣን ይሆናል። ፍላጎት በመጨመሩ ምክንያት እጅግ ከፍተኛ የጥሪ መጠን እያጋጠመን ሲሆን ብዙ ደንበኞች ማለፍ አልቻሉም።
- ከዚህ በታች ከመደበኛው የተጠቃሚ የስራ እጥነት ኢንሹራንስ (Unemployment Insurance, UI) ሳምንታዊ የይገባኛል ጥያቄዎች በተጨማሪ የወረርሽኝ ሥራ አጥነት ድጋፍ (Pandemic Unemployment Assistance, PUA) አመልካቾች የጥያቄዎችን ብቁነት ለማረጋገጥ ተጨማሪ ጥያቄዎችን መመለስ አለባቸው። ይህ የፌዴራል ሕግ ግዴታ ነው።

**ወደ PUA የብቁነት ጥያቄዎች እና መመሪያ ገጽይሂዱ።**

## ሳምንታዊ የይገባኛል ጥያቄዎን በተመለከተ የምንጠይቃቸው ጥያቄዎች

ሳምንታዊ የይገባኛል ጥያቄዎን በሚያቀርቡበት ጊዜ የምንጠይቃቸው ጥያቄዎች በመስመር ላይም ሆነ በስልክ ሲያስገቡ ተመሳሳይ ናቸው።

- በየቀኑ በአካል ብቁ እና ለስራ የሚገኙ ነዎት?
  - በCOVID-19 ምክንያት በንግድ ሥራ መዘጋት ምክንያት ሥራ ፈት ከሆኑ ወይም በCOVID-19 የመያዝ ከፍተኛ ስጋት ካለብዎት እና እራስዎን ለብቻዎ እንዲያገለሉ ምክር ከተሰጠዎት አሁንም ለዚህ ጥያቄ "አዎ" የሚል መልስ መስጠት አለብዎት።
- አሁን ይገባኛል በሚጠይቁት ሳምንት ውስጥ መመሪያው እንዳስቀመጠው ንቁ የሥራ ፍለጋ አድርገዋል?
- የተጠባባቂነት ጥያቄዎ እስካልተረጋገጠ ድረስ የሥራ አጥነት ጥቅሞችን መቀበል ሥራን በንቃት እንዲፈልጉ ይጠይቃል።
  - **በCOVID-19 ወረርሽኝ ወቅት የሥራ ፍለጋ መስፈርቶችን ሲሞሉ እርስዎን ለማገዝ አንዳንድ አስተያየቶች እነሆ:-**

- በ WorkSourceWA.com በኩል ለሥራ ያመልክቱ።
- ማመልከቻዎችን ጥቂቶቹን ለመጥቀስ እንደ Indeed, CareerBuilder እና Monster ባሉ የፍለጋ ፕሮግራሞች በኩል ያስገቡ።
- እየቀጠሩ እንደሆነ ለሚያውቋቸው አሠሪዎች ስላላቸው የሥራ እድሎች መደወል።
- በ WorkSource የተሰጡትን ምናባዊ አውደ ጥናቶችን ማጠናቀቅ።
- **ማሳሰቢያ፡-** እርስዎ የሚያመለክቷቸው ሥራዎች እርስዎ ቀደም ብለው ልምድ፣ ሥልጠና ወይም ትምህርት የወሰዱበት መሆን አለባቸው። ይህ እንደ ተስማሚ ሥራ ይታያል።
- እኛ ሳምንታዊ የሥራ አጥነት ብቁነትን በምንወስንበት ጊዜ የሥራ ፍለጋ መስፈርቶችን ለማጠናቀቅ የተደረጉትን ጥረቶች ሁሉ ከግምት ውስጥ እናስገባለን።

- ስለ ንቁ የሥራ ፍለጋ ጥያቄ "አዎ" የሚል መልስ ከሰጡ እና ከሥራ ፍለጋ መስፈርቶችዎ ካልተገለሉ ተጨማሪ ጥያቄ ይጠየቃሉ። በየሳምንቱ ተገቢውን የአሰሪ ግንኙነቶች ወይም በአካል ያሉ እንቅስቃሴዎችን (በ WorkSource ወይም በሌላ ግዛት ውስጥ ባለ American Job Center እንዳደረጉ እና ይህንን መረጃ በስራ ፍለጋ መዝገብዎ ላይ እንደመዘገቡ ማረጋገጥ አለብዎት።
- ከክልል ውጭ ያሉ አመልካቾች በየሳምንቱ ለሚጠየቁ ይግባኞች የሥራ ፍለጋ ግንኙነቶችን ለመመዝገብ ዝግጁ መሆን አለባቸው።
- ለአሠሪ እውቂያዎች፣ ለሚደረጉ እያንዳንዱ ግንኙነቶች ከሥራ-ፍለጋ መዝገብዎ የሚከተሉትን ንጥሎች እንዲያቀርቡ ይጠየቃሉ፡- ቀኑን፣ የንግድ ሥራ ስም እና የተሟላ አድራሻ፣ የንግድ ስልክ ቁጥር ወይም ኢሜይል፣ ግንኙነቱ እንዴት እንደተደረገ፣ ያነጋገሩት ሰው እና እየይፈለጉ የነበረው የሥራ ዓይነት።
- በአካል ለሚደረጉ እንቅስቃሴዎች (በ WorkSource ወይም በሌላ ግዛት ውስጥ ባለ American Job Center) ለእያንዳንዱ እንቅስቃሴዎ ከሥራ ፍለጋ መዝገብዎ ውስጥ የሚከተሉትን እንዲያቀርቡ ይጠየቃሉ፡- ቀኑን፣ ቢሮውን እና የእንቅስቃሴውን መግለጫ።
- ማንኛውንም የሥራ አቅርቦትን እምቢ ብለዋል አልያም ለታቀደ የሥራ ቃለ መጠይቅ ሳይሄዱ ቀርተዋል?
- ለሠራተኞች ወይም የወንጀል ሰለባ ለሆኑ ካሳ አመልክተዋል ወይም ተቀብለዋል?*
- በጡረታ ላይ ለውጥ አለዎት ወይም አመልክተዋል?*
- ከመደበኛ ቀጣሪዎ ከሳምንቱ ለየትኛውም ቀን የባኣል ክፍያ ተቀብለው ያቃሉ ወይም ይቀበላሉ? *
- እርስዎ ይገባኛል ለሚጠይቁት የሳምንቱ ማንኛውም ቀን ከመደበኛ አሠሪዎ የእረፍት ክፍያ ተቀብለዋል ወይም ይቀበላሉ?*
- እርስዎ ይገባኛል ለሚጠይቁት የሳምንቱ ማንኛውም ቀን በማስጠንቀቂያ ወይም በማቋረጥ ክፍያ ምትክ ደመወዝ ተቀብለዋል ወይም ይቀበላሉ?*
- በዳኝነት ላይ አገልግለዋል?*
- በተከታታይ ከ72 ለሚበልጡ ሰዓታት በወታደራዊ ሪዘርቭ ወይም በብሔራዊ ጥበቃ ውስጥ ሥራ አከናውነዋል?*
- የራስዎን ሥራ ሰርተዋል?*
- ባለፈው ሳምንት ለማንኛውም አሰሪ ሰርተዋል?*

*** በተቀበሉበት ሳምንት ሳይሆን ያገኙበትን ሳምንት ገቢ ሪፖርት ያድርጉ።** ከመቀነሱ በፊት ጠቅላላውን መጠን ያሳውቁ። ለግል ሥራ የተጣራ ገቢዎን ያሳውቁ። እንዲሁም እርስዎ ገቢ ያገኙበትን ጠቅላላ ሰዓት ወይም ቀናት ይጠየቃሉ።

## ገቢ መቀነሻ ገበታ

ከሳምንታዊ የይገባኛል ጥያቄዎ ምን ያህል እንደሚቀረጥ ለማወቅ እንዲረዳዎ የአሁኑን የገቢዎች ቅነሳ ሰንጠረዥ(Earnings Deduction) ማውረድ ይችላሉ።

## በሳምንቱ ውስጥ ከሰሩ የሚከተሉትን ለማቅረብ ዝግጁ ይሁኑ፡-

- ምንም እንኳን ገና ያልተከፈለዎት ቢሆንም በዚያ ሳምንት ያገኙት መጠን። (ገቢዎች ደመወዝ፣ ኮሚሽኖች እና ጉርሻዎችን ጨምሮ ለግል አገልግሎት ያገኙትን ሁሉንም ካሳ፣ ከገንዘብ ውጭ በማንኛውም መንገድ የሚከፈለው የካሳ የጥሬ ገንዘብ ዋጋ እና የተጨማሪ ክፍያዎች ተመጣጣኝ ዋጋን ያጠቃልላል።)
- በሳምንቱ ውስጥ ምን ያህል ሰዓታት እንደሰሩ።
- የአሰሪዎ የንግድ ስም።
- የአሠሪዎ የተሟላ የንግድ አድራሻ።
- በዚህ ሳምንት ሥራ የጀመሩበት ቀን።

## ገቢዎችዎን ካስገቡ በኋላ

“በሚቀጥለው ሳምንት ለተመሳሳይ አሠሪ እንደሚሰሩ ይጠብቃሉ?” ተብለው ይጠየቃሉ። አይ ብለው ከመለሱ ምክንያቱን መጥቀስ አለብዎ፡-

1. የሥራ እጥረት
    - ለምሳሌ ያ አሠሪ በCOVID-19 ወረርሽኝ ወቅት በንግድ ወይም በሕዝብ ጤና መመሪያ መጥፋት ምክንያት ሥራውን ዘግቷል ወይም ሰራተኞች ቀንሷል።
2. በሥራ እጥረት ምክንያት የተቀነሱ ሰዓቶች
3. መባረር
4. እርስዎ አቋመዋል
5. ሌላ ምክንያት

## ሌላ ሊመዘገብ የሚችል ገቢ አለዎት?

ገቢዎ በሪፖርት የሚቀርብ መሆኑን እርግጠኛ ካልሆኑ ለሥራ አጥነት ሠራተኞች መመሪያ መጽሐፍ(Handbook for Unemployed Workers) (PDF፣ 2.9MB) ውስጥ ከገጽ 27-28 ያለውን ከዚህ በታች ያለውን ዝርዝር ይመልከቱ።

መልሶችዎን ሲያጠናቅቁ ስርዓቱ "**የይገባኛል ጥያቄዎ ተቀባይነት አግኝቷል (Your claim has been accepted)።**" የሚል መልእክት ይናገራል ወይም ያሳያል።

**ሪፖርት የሚደረጉ ገቢዎች የሚከተሉትን ያጠቃልላሉ፡-**

1. ከራስዎ ንግድ የተጣራ ገቢ።
2. እንደ ኪራይ ወይም ክፍል እና ቦርድ ያሉ ገንዘብን የሚተኩ የዓይነት ክፍያዎች።
3. በዚያ ሳምንት ውስጥ ለተከናወኑ ሥራዎች የተሰጡ ጉርሻዎች።
4. ተጨማሪ ክፍያዎች በማንኛውም መልኩ
5. የተከፈለ ዕረፍት፣ በዓላት እና የሕመም እረፍት።

6. በተከታታይ ከሶስት ቀናት በላይ ከሠሩ ወታደራዊ ሪዘርቭ እና ብሔራዊ ጥበቃዎች ይከፍላሉ።
7. ለዳኝነት ግዴታ አገልግሎት ይከፈሉ።
8. ከግዛት ሥራ ጥናት የተገኙ ገቢዎች (የርዕስ IV ገንዘብን አያካትትም)።
9. ይግባኝ ከጠየቁባቸው ሳምንቶች እንደ የኋላ ክፍያ (እንደ የጠፉ ጊዜ ወይም የሠራተኞች ካሳ ጥያቄን ጨምሮ) ከአሰሪ ይከፈሉ።

### ሳምንታዊ የይገባኛል ጥያቄዎ ላይ ስህተት ከሰሩ

ሳምንታዊ የይገባኛል ጥያቄዎን በሚያቀርቡበት ጊዜ ስህተት ከፈፀሙ ብለው ከመስማት ወይም ከማየትዎ በፊት በማንኛውም ጊዜ ሊጀምሩ ይችላሉ፣ "**የይገባኛል ጥያቄዎ ተቀባይነት አግኝቷል።**" የይግባኝ ጥያቄዎን በሚያቀርቡበት ጊዜ በአብዛኛዎቹ ጉዳዮች ላይ ስህተቶችን ለማረም እድል ይኖርዎታል።

ሳምንታዊ የይገባኛል ጥያቄዎን ካቀረቡ ***በኋላ*** ስህተትዎን ካወቁ የይገባኛል ጥያቄ አቅራቢውን መጥራት እና ማነጋገር ያስፈልግዎታል። ስህተቱን ለማስተካከል 800-318-6022 ይደውሉ። ለአሁኑ የይገባኛል ጥያቄዎች ማዕከል የእውቂያ መረጃ እና ሰዓታት ወደሚከተለው ይሂዱ፡- https://esd.wa.gov/unemployment/unemployed-workers-contact

**ስህተቶችዎን ለማረም የይገባኛል ጥያቄ አቅራቢዎችን ማዕከል መጥራት አለመቻልዎ ከመጠን በላይ ክፍያ ሊያስከትሉ እና ጥቅሞችዎ ሊከለከሉ ይችላሉ።**

# በእርስዎ PUA ሳምንታዊ የይገባኛል ጥያቄ ላይ የምንጠይቃቸው ጥያቄዎች

እነዚህ ጥያቄዎች አንድን ሰው ለPUA ብቁ የሚያደርጉ የCOVID-19 ምክንያቶች ናቸው። ጥያቄዎቹን በሐቀኝነት ይመልሱ። እነሱ CARES(Coronavirus Aid, Relief, and Economic Security), የኮሮናቫይረስ ዕርዳታ፣ የእርዳታ እና የኢኮኖሚ ደህንነትህግ) ህግ የተጠየቁ ሲሆን የይገባኛል ጥያቄዎች በአሜሪካ የሰራተኛ መምሪያ (U.S. Department of Labor) ኦዲት ሊደረጉ ይችላሉ። ከእንግዲህ ለPUA ብቁ ካልሆኑ ለመደበኛ የሥራ አጥነት ጥቅሞች እንደገና ለማመልከት ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ።

እነዚህ ጥያቄዎች የሚመለከቱት እርስዎ ይግባኝ ለሚጠይቁበት ሳምንት ብቻ ነው። እነሱ ከ UI ሳምንታዊ የይገባኛል ጥያቄዎች በተጨማሪ ናቸው። እነሱ አዎን ወይም አይ ተብለው ሚመለሱ ጥያቄዎች ናቸው። የእኛ የCOVID-19 *ሥራ አጥነት መመሪያ* ለእነዚህ ጥያቄዎች መልስ ለመስጠት የበለጠ መረጃ ይሰጣል። ከ ገጽ 28 ጀምሮ።

eServices በመጠቀም የPUA ሳምንታዊ የይገባኛል ጥያቄዎን በኤሌክትሮኒክ መንገድ ካቀረቡ እነዚህን የብቁነት ጥያቄዎች በመስመር ላይ መመለስ ይችላሉ። በራስ-ሰር የስልክ ስርዓታችን በመጠቀም ጥያቄዎን ካቀረቡ ወዲያውኑ መሙላት እና ወዲያውኑ መመለስ ያለብዎትን መጠይቅ እንልክልዎታለን። ለPUA ብቁ እንደሆኑ እንዲቀጠሩ የእርስዎን ምላሾች መቀበል እና መልሶችዎን ማስኬድ አለብን። መልስዎን በምንጠብቅበት ጊዜ ጥቅማጥቅሞችዎን በሁኔታዎች ልንከፍል እንችላለን፣ ግን ለጥያቄው መልሶችዎን ካልተቀበልን መልሰው መክፈል ይኖርብዎታል። **ሳምንታዊ የይገባኛል ጥያቄዎን በስልክ ካቀረቡ ጥያቄዎቹ በጥቂቱ ሊለያዩ ይችላሉ። የሚቻል ከሆነ የPUA ሳምንታዊ የይገባኛል ጥያቄዎን በ eServices ውስጥ እንዲያቀርቡ አጥብቀን እንመክራለን።**

## የPUA የብቁነት ጥያቄዎች እና መመሪያ

የስራ ቅጥር ዋስትና መምሪያ እኩል ዕድል የሚሰጥ ቀጣሪ/ፕሮግራም ነው። አካል ጉዳተኞች በሚያቀርቡት ጥያቄ መሰረት አጋዥ መሳሪያዎችና አገልግሎቶች ይቀርባሉ። የእንግሊዝኛ ቋንቋ ውስንነት ላለባቸው ሰዎች የቋንቋ ድጋፍ አገልግሎቶች ከክፍያ ነጻ ይቀርባሉ። የዋሽንግተን ማስተላለፊያ አገልግሎት (Washington Relay Service)፡ 711